DC | HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# ደረጃ ሁለት መመሪያ

# Coronavirus2019(COVID-19): የጋራ መጓጓዣ (የኪራይ መኪናዎች፣ታክሲ እና መኪና የሚጋሩ)የወጡ መመሪያዎች

**በደረጃ ሁለት ጊዜ ወሳኝ ያልሆኑ የጋራ ማጓጓዣዎች ሊቀጥሉ ይችላሉ።** ማህበረሰቡ እና የንግድ ማዕከሎች አዳዲስ አካሄዶችን እና እራሳቸውን ከሚያጋልጡ ነገሮች እንዲጠብቁ ያስፈልጋል። በደረጃ ሁለት አገልግሎት **የሚሰጡ ኪራይ መኪናዎች፣ታክሲ እና መኪና የሚጋሩ የወጡ መመሪያዎች ለተቀጣሪዎች/ሹፌሮች፣ለተሳፋሪዎችና ለማህበረሰባችን የኮቪድ-19 በሽታ ስርጭትን ለመቀንስ የሚረዱ ናቸው።** ለተጨማሪ መረጃ coronavirus.dc.gov/phasetwo ማየት ይችላሉ.።

ሌሎችን ላለመበከል ሲባል የኮቪድ-19 ምልክቶች የሚያሳዩ ግለሰቦች ወይም በቅርብ ቀናት ውስጥ በኮቪድ-19 የተያዘ ሰው ወይም የተጋለጠ ሰው የኪራይ መኪናዎች፣ታክሲ እና የጋራ መኪናዎች ላይ ስራ መስራት የለባቸውም። የኮቪድ-19 ምልክቶች ይህንን ያካትታሉ፡- ትኩሳት(100.4 ዲግሪ ፋራናይት ውስጥ ከሆነ)ብርድ ብርድ ስሜት፣ በሚተነፍሱበት ጊዜ የመቆራረጥ ወይም ለመተንፈስ የሚያስቸግር ከሆነ፣ድካም፣የጡንቻና የሰውነት አካል ህመሞች፣ራስ ምታት፣ የመቅመስና ማሽተት ስሜትን ማጣት፣የጉሮሮ ህመም፣ንፍጥ ወይም ከአፍንጫ የሚወጣ ፈሳሽ፣ማቅለሽለሽ ወይም ማስመለስ፣ተቅማጥ፣ወይም ጥሩ ስሜት ያለመሰማት

## ሹፌሮችና ደንበኞች በየቀኑ በሽታውን ለመከላከል የሚረዱ እርምጃዎችን መተግበር

- **ከታመሙ** ወይም በቅርብ ጊዜ ኮቪድ-19 ላለበት ሰው ከተጋለጡ **ቤት ይቆዩ።**
- በጣም ወሳን እስካልሆነ ድረስ ደንበኞች ታማሚ ሆነው የኪራይ መኪናዎችን ፣ታክሲዎችን ወይም የጋራ መኪናዎችን እንዳይጠቀሙ ፣ተደርበውም እንዳይጫኑ ።
- በተቻሎት መጠን ከሌሎች ሰዎች ቢያንስ 6 ጫማ ያህል ይራቁ።
- ሹፌሮች እና ደንበኞች ሁልጊዜ የፊት መሸፈኛ ጨርቅ ማድረግ አለባቸው።
- ደንበኞች የራሳቸውን እቃ በራሳቸው መያዝ አለባቸው።በተቻለ መጠንም ንክኪ የሌለውን የአከፋፈል ዘዴ ይጠቀሙ።
- ተደጋጋሚ የእጅ ንጽሕናን ያከናውኑ (በሳሙና እና በውሃ ወይም በአልኮል ላይ የተመሠረተ የእጅ መታጠቢ)።
    - የእጅ ንፅህናን ለማከናወን ቁልፍ ጊዜዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:
        - ምግብ ከሙብላትዎ በፊት
        - ሽንት ቤት ከተጠቀሙ በኃላ
        - የጨርቅ የፊት ሽፋኖችን ከመልበስዎ፣ ከመንካትዎ ወይም ከማስወገድዎ በፊት እና በኋላ፣
        - ከስራ ፈረቃ እና የስራ ዕረፍት በፊት እና በኋላ፣
        - በጉዞዎች መካከልና ገንዘብ ከተለዋወጥን በኃላ
        - ነዳጆችን ከመሙላታችን በፊትና በኃላ
        - አይቀሬ ሆኖ የደንበኛ እቃ ከነካኩ በኃላ እና
        - አፍንጫዎን ከተናፈጡ፣ ካሳሉ ወይም ካስነጠሱ በኋላ።
- ሹፌሮች በመኪናቸው ውስጥ የሶፍት ወረቀት ሊኖራቸው ይገባል። ደንበኞች እና ሹፌሮች መኪና ውስጥ ካሳሉ ወይም ካስነጠሱ አፍና አፍንጫቸውን መሸፈን አለባቸው፣እጃቸውን ካፀዱ በኃላ የተፀዳዱበትን ቆሻሻ መጣያ ውስጥ መጣል አለባቸው።
- ጓንት በተለመደው የሥራ ኃላፊነት በተጠቀሰው መሠረት መደረግ አለበት።

- ደንበኞች በወጡት መመሪያዎች የጥንቃቄ መመሪያዎች መሰረት የማይስተናገዱ ከሆነ ይህን ጉዳይ ለአስተዳደር፣ለድርጅትዎ እና/ወይም ህጋዊ ስልጣን ላላቸው እንደ አስፈላጊነቱ መጠቆም ይችላሉ።
- ለጥንቃቄ ብሎ በግልፅ ለታመመ ሰው የትራንስፖርት አገልግሎት ላለመስጠት መምረጥ ይችላሉ። ይሁን እንጂ በዘር፣ በትውልድ ቦታ የሚደረጉ መድሎዎች ወይም በሌሎች የኩባንያው ፖሊሲ፣የአካባቢ፣የክልል እና የፌደራል ህጎች መሰረት ተቀባይነት አይኖራቸውም።

## የሹፌሮችና የደንበኞችን ደህንነት ለማበረታታት ሲባል ቀጣሪዎችና/ሹፌሮችን የተመለከተ አሳቤ

- ለሹፌሮችና ሌሎች ተቀጣሪዎች የእጅ ንፅህናቸውን ቶሎ ቶሎ ለመጠበቅ የሚያስችሉ ቁሳቁሶችን ማቅረብ(ለምሳሌ ሳሙና እና ዉሀ ወይም 60% አልኮል ይዘት ያላቸው ሳኒታይዘሮችን) በየመኪናዎቹና በቢሮ ስራ ቦታዎችና በጋራ የሚጠቀሙባቸው ቦታዎች ላይ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡
- ለሰራተኞች ተገቢውን የሰውነተ መከላከያ ቁሳቁሶችን(ለምሳሌ ጭንብሎችን)እና የፊት መሸፈኛዎችን ማቅረብ፡፡
- ተለዋዋጭ እና ቅጣትን የማያሳዩ የመልቀቂያ ፖሊሲዎችን ይተግብሩ ፣ እንዲሁም የታመሙ ሰራተኞች ቤት እንዲቆዩ ይፍቀዱ ፡፡
    - የቤተሰብ አባል የሚያስታምሙ ወይም የልጆቻቸው ትምህርት ቤት ወይም ህፃናት ማቆያ የተዘጉ እንደሆነ የሰራተኛ ከስራ ዕረፍት የመውሰድ ፖሊሲው ይህንን ማካተት ይጠበቅበታል፡፡
- በተቻለ መጠን የፈረቃ ቅይይሮች፣ስራ መጀመሪያ ሰዓቶችና የዕረፍት ሰዓቶች
- በሹፌሮችና ተሳፋሪዎች መካከል እስኪብርቶና ኤሌክትሮኒክስ ፓዶችን በመጠቀም የሚደረጉ ፊርማዎችና የገንዘብ አከፋፈል ላይ ግንኙነት እንዳይኖር ፖሊሲዎችና ቴክኖሎጂዎችን ማሳደግ ይህም ንክኪን ለመቀነስ ወይም ለማጥፋት ይረዱናል፡፡
- ስለ COVID-19 ተቀጣሪዎቹን ማስተማር ለበለጠ መረጃ coronavirus.dc.gov ይመልከቱ፡፡
- የጋራን መጓጓዣ በተመለከተ ለበለጠ መረጃ የሲዲሲ ድህረ ገፅ ይመልከቱ፡-cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/community/organizations/rideshare-drivers-for-hire.html

## ለበሽታው ምልክቶች ማጣራት እና መከታተል

- በስልክ ወይም በአካል በየቀኑ ስራ ከመጀመሩ በፊት የሰራተኞችን የጤና ሁኔታ ማጣራትን ያካሂዱ (ለምሳሌ የምልክት መጠይቆችን በማዘጋጀት )
- በቢዝነሱ መግቢያ ላይ የማጣራት ሂደቱን በተመለከተ ሰራተኞችን እና እንግዶችን የሚያስረዱ ምልክቶቹን ያስቀምጡ፡፡
- አንድ ሰራተኛ ስራ ላይ እያለ የኮቪድ-19 ምልክቶችን ካሳየ ያሰራተኛ እንዴት እራሱን ማግለል እንዳለበት፣ ለጋራ መጓጓዣው ኃላፊው ማሳወቅ እንዳለበትና አገልግሎቱን ትቶ መውጣት እንዳለበት የተቀመጠ እቅድ መኖር አለበት፡፡
- ቢያንስ ለሰላሳ ቀናት ያህል በመስሪያ ቤቱ ያሉትን ግለሰቦች እና የደንበኞችን መዝገብ ይኑሮት፡፡

## ቅርብ ግንኙነትን ያስወግዱ እና የመነካካት ነጥቦችን ይቀንሱ

- ደንበኞች ጋቢና ከሹፌሩ አጠገብ እንዳይቀመጡ መከልከል
- የተሳፋሪዎችን ቁጥር በ 1 ወይም የአንድ ቤተሰብ አባላት ብቻ አድርገው ይውሰዱ፡፡
  ሊፈቀድላቸው የሚችል ወሳኝ አብሮ የሚሆን የግል አጋዥን የመሰሉ ሰዎች ናቸው፡፡
- የሹፌሩንና የተሳፋሪውን መቀመጫ መከፋፈል ያስፈልጋል፡፡
- በተቻለ መጠን ከደንበኞች ጋር ያለውን የቅርብ ንክኪ ያስወግዱ፡፡
    - ከመኪናው ውጪ ሲሆኑ ከደንበኞች ጋር ቢያንስ የ6 ጫማ ርቀት ይኑሮት፡፡
    - ሲጭኗቸው እና ካደረሷቸው በኃላ ደንበኞች የራሳቸውን ንብረት እና ሻንጣዎች እራሳቸው ጭነው እንዲያወርዱ ይጠይቁ፡፡ ይህ ካልሆነ ደግሞ የእጃችንን ንፅህና መጠበቅ
- ተሳፋሪ መኪና ውስጥ በሚኖርበት ጊዜ አየር ታምቆ እንዳይቆይ ማድረግ፡፡ የመኪናውን የአየር ማጥሪያ መጠቀም ወይም ንፁህ አየር እንዲገባ መስኮቶቹን ዝቅ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

- የውሀ ጠርሙሶች ወይም መፅሔት የመሰሉ ነገሮችን አይስጡ፡፡
- የበር መከፈቻዎች፣መስኮቶች፣የደህንነት ቀበቶዎች፣መሪ፣ማርሾች፣ምልክት መጠቆሚያዎች እና ማንኛውም የመኪናው አካል ከመፅዳቱና ፀረ ተዋህሲያን ከመረጨቱ በፊት ተሳፋሪ ወይም ሌሎች ሹፌሮች በተደጋጋሚ ከሚነኩ ገፅታዎች እራሳቸውን መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡
  መከፈቻዎች እና ወይም ሌሎች የመኪናው አካላቶችን ከመጠቀማችን በፊት ማፅዳትና ፀረ ተዋህሲያንን መርጨት ያስፈልጋል፡፡

## ያጽዱ እና ከጀርም ያስወግዱ

- ቢያንስ በተደጋጋሚ የሚነካኩ የመኪና ገፅታዎችን በመነሻና በመድረሻ ቦታዎች፣እና የታመመ ተሳፋሪን ከያዙ በየመሀከሉ ማፅዳትና ከተዋህሲያን ነፃ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- ፀረ-ተዋህሲያንን መርጨት ወይም በሶፍት መወልወልና የቆሻሻ ማስቀመጫ ቦርሳዎችን መኪና ውስጥ ማስቀመጥ ይኖርብናል፡፡ ፀረ-ተዋህሲያኑን ከምርቱ ወረቀት ላይ አጠቃቀሙን መከተል
- የአቧራ ገፅታ ካለው በሳሙና ምርቶች ወይም ሳሙና እና ውሀን በመጠቀም ከ ተዋህሲያን ነፃ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- ቢያንስ በተደጋጋሚ የሚነካኩ የመኪና ገፅታዎችን በመነሻና በመድረሻ ቦታዎች፣እና የታመመ ተሳፋሪን ከያዙ በየመሀከሉ

ማፅዳትና ከተዋህሲያን ነፃ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

- ደንበኛ ከመግባቱ በፊት በቂ ሰዓትን ወስዶ ማፅዳትና ፀረ ተዋህሲያንን መርጨት ያስፈልጋል፡፡
- ኮቪድ-19ን በስርዓቱ ስለሚያስወግዱ ፀረ ተዋህሲያን የበለጠ መረጃ ከፈለጉ የሲዲሲን ድህረ ገፅ cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/community/reopen-guidance.html ይጎብኙ፡፡
- ለበለጠ መረጃ ማጽዳት እና ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ ለማድረግ 2]cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/community/reopen-guidance.html ይህንን ይመልከቱ፡፡

## ለኮቪድ-19 ተጋላጭ ለሆኑ ዕቅድ ያውጡ

- ሰራተኛው/ሹፌሩ ወይም ደንበኛው የኮቪድ-19 ህክምና ላይ ከሆነ የወጣ ዕቅድ
- አንድ ተቀጣሪ/ሹፌር በኮቪድ-19 ተይዞ መያዙን ማሳወቅ ከፈለገ በድርጅቱ ሄዶ የሚያሳውቅበትን ቦታ ለይተው ያሳውቁ፡፡
- አንድ ሰራተኛ/ሹፌር ለሚሰራበት ቦታ በኮቪድ-19 መያዙን ማሳወቅ ከፈለገ መስሪያቤቱ የሚከተሉትን ለሌሎች ሰራተኞች ለማካፈል ሲባል የአሰራር ዘዴ መዘርጋት አለበት፡፡
    - ስለኮቪድ-19 ግንዛቤን መፍጠር ይህም የኮቪድ-19 ምልክቶችን ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡
    - ስለ ኮቪድ-19 ሰዎች የበለጠ ማወቅ ከፈለጉ coronavirus.dc.gov እዚህ ላይ ያገኛሉ፡፡
    - በኮሎምቢያ አውራጃ የሚገኘውን የኮቪድ-19 ምርመራ መረጃ coronavirus.dc.gov/testing እዚህ ላይ ያገኛሉ፡፡
- ሰራተኛው ሲመረመር ኮቪድ-19 ከተገኘበት ሰው ብዙ ግንኙነት ከደንበኛ ጋር የነበረው ከሆነ ወይም ደንበኛው ሲመረመር ኮቪድ-19 ከተገኘበት ለዲሲ የጤና ማዕከል ከነዚህ መረጃዎች ጋር coronavirus@dc.gov በዚህ ኢሜይል ማሳወቅ ይኖርቦታል፡፡
    - 'ሰብጀክት' በሚለው ቦታ ላይ "COVID-19 Consult" ብለው ይላኩ
    - ዲሲ ጤና መልሶ እንዲደውል በድርጅቱ በቀጥታ ማግኘት የሚችለውን ስልክ ቁጥርና ሰው ስም እና ቁጥር
    - ሊጋለጡ ይችላሉ ብሎ የገመቱትን የደንበኛ ብዛት ማሳወቅ
    - የተፈጠረውን ሁኔታ በአጭሩ ይግለፁ
- በአግባቡ ለተላኩ ኢሜሎች በ48 ሰዓት ውስጥ አንዴ የዲሲ ጤና መርማሪ መልስ ይሰጥበታል፡፡

ከዚህ በላይ ያሉት መመሪያዎች ይህ እስከሚወጣ ድረስ ያሉትን ሁሉ ያካተተ ነው፡፡ እባክዎን coronavirus.dc.gov ለወቅታዊ መረጃ በመደበኛነት ይጎብኙ።